# ፋሊስ

ዙፋኑ የየትኛውም ሥርዓት የዑደቱ ማዕከልና የሥልጣን ምንጭ ሆኖ ያገለግላል

ተመስገን ጌታሁን



# ፋሊስ

በ

ተመስገን ጌታሁን

መጋቢት፣ 2013 ዓ.ም

© ተመስገን ጌታሁን ከበደ 2013 ዓ.ም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

አድራሻ
ተመስገን ጌታሁን ከበደ
Email:temesgengt@gmail.com
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# መግቢያ

ኢትዮጵያዊ ሆኜ ኢትዮጵያን የጠላሁበት ጊዜ ነበር። ለጥላቻዬም ምላሽ የመንግሥት ተቀጣሪነት ሥራዬን በገዛ ፈቃዴ ለቀቅኩ። ከደመወዜ የተረፈችኝን ሀያ ሰባት ብር ከምናምን ሳንቲም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሥላሴ ቅርንጫፍ አውጥቼ ደብተሩን ለባንኩ መለስኩ። "የዚችን አገር ባህልና ወግ፣ አፍ የፈታሁበትን ቋንቋ ሁሉ ከመጥላቴ የተነሣ አእምሮዬ ላይ የተከተበውን ትውስታ አንድ በአንድ የሚሰርዝ ልዩ ጥበብ በኖረና ኢትዮጵያዊነቴን መርሳት ብችል" ብዬ በጽኑ ተመኘሁ። ሐበሻን ሁሉ ጠላሁት፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ጠላኋቸው።

እነዚያ የዝምታ ሰባት ዓመታት የረዘሙብኝ የሰባት ሺህ ዓመታትን ያህል ነበር። እያንዳንዷ ሴኮንድ ቀጥ ብላ እንደቆመች ይሰማኝ ነበር። "ጸሎት ለጥላቻ ፈውስ ይሆን?" ብዬ ከራሴ ጋር መከርኩና ለጸሎት ተንበረከኩ። ሲሚንቶው ጋር የተጣበቀው ጉልበቴ ደደረ። ውስጤም ምንም እንዳልተጻፈበት ንጹሕ ጽላት (clean slate) ባዶነት ረበበበት። ልቤ፣ አንደበቴም የምስጋናም ሆነ የምሬት ቃል ማውጣት ተሳናቸው። የእግዚአብሔር ዝምታም በላዬ ላይ እጅግ በረታ። በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንደሚራመድም ሰው መባዘን ተረፈኝ። ቢጨንቀኝ አጠገቤ ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ

ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው መሥመር አነበብኩት፡፡ እጅግ አድርጌ የጠላኋት ኢትዮጵያ በየምዕራፎቹ መካከል ብቅ እያለች አበሳጨችኝ፡፡ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ስትዘረጋ፤ ሁከት በኢትዮጵያ ምድር ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፤ ንጉሧ እስራኤልን ሊወጋ አንድ ሚሊዮን ጦር ሲያዘምት፤ ኢትዮጵያውያኑም ፈጽመው እስኪጠፉ ሲወድቁ፤ እንደ ነብርም ዝንጉርጉርነታቸውን መልቀቅ ሳይችሉም ተመለከትኩ፡፡ በብሉይ ኪዳን 44 ጊዜ፤ በ2ኛው ቀኖና 10 ጊዜ፤ በሐዲስ ኪዳን 2 ጊዜ፤ በድምሩ 56 ጊዜ "ኢትዮጵያ" ከሚለው ስም ጋር ተፋጠጥኩ፡፡ ፍለጋዬ ከኢትዮጵያዊነት የሚገላግለኝን ነገር ለማግኘት ብቻ ነበር፡፡ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ ኢትዮጵያን በሸሸኋት ቁጥር በአእምሮዬ ውስጥ እየገዘፈችብኝ ብስጭቴም እየጨመረ ሄደ፡፡

በዚያ ልገልጸው በማልችለው የጥላቻ ሕመም ዘመኔ ከዓለም ጥግ ያሉ ወዳጆቼ በአንዳች ኃይል ተገፍተው ሲያስታውሱኝ እጅግ ገረመኝ፡፡ በአእምሮው ውስጥ እየተመላለስኩበት ሻይ አላስጠጣ ያልኩት ካናዳ የሚኖረው ኢትዮጵያን በልቡ ይዟት የተሰደደው አብሮ አደግ ጓደኛዬ ሰሎሞን ጣዕመ "ተማው ምነው ልቤ ስለአንተ እረፍት አጣ?"፤ ሎንዶን የሚኖረው ኢራናዊው ወዳጄ ሐሚድ ማሊክ ናስር "ለምን ይሆን ስለአንተ ማሰብ ማቆም ያልቻልኩት?" ሲሉኝ ሰውነቴን ነዘረኝ፡፡ ሕመሜን ማን ነገሯቸው "አይዞህ፤ አለንልህ" አሉኝ? አምርሬ ከጠላሁት ሐበሻ መካከል ዶክተር ቴዲ እንዴት እንደሆነ ባላውቅም ሳይታክት የፋይናንስ ድጋፍ እያደረገልኝ ክፉ ቀኔን አሻገረኝ፡፡ "ደብተራው" እያልኩ የምጠራው ጓደኛዬ አያሌው ረዴ በእነዚያ ክፉ ቀኖቼ ከጎኔ ነበር፡፡ እረፍት አጥቶ ስለእኔ ይጨነቅልኝ የነበረውን ደምመላሽን ፈጽሞ አልረሳውም፡፡ ከሁሉ ሁሉ ልጄ ብርሃኔ ተመስገን ግን የእፎይታዬ

ሁሉ ምንጭ ነበረች። በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ወድቄ እንዳልቀር እነዚህና ሌሎች በርካታ ወዳጆቼ እንደ ብርሃን ፋና እየመሩ ክፉ ቀኔን አሻግረውኛል። ለእነዚህ ሁሉ ምስጋና ይግባቸው።

ይህንን ሁሉ አሳሬን ሳይ ጦርነት (War) ከአእምሮ የሚፈልቅ፣ የውጊያ ሜዳ (Battle Feild) በልብ ውስጥ የሚፈጠር መሆኑን መቼ አውቄ። በጦርነት አሸናፊና ተሸናፊ እንደሌለ መቼ ገብቶኝ፣ የሚቋጨውም በስምምነት ብቻ መሆኑን መቼ ተረድቼ። ለካ መሸነፍና ማሸነፍ ያለው በውጊያ ሜዳ ብቻ ነው። አእምሮዬ ላያሸንፍ ወይም ላይሸነፍ ከኢትዮጵያ፣ ከነገሥታቱ፣ ከሐበሻም ጋር ጦርነት መግጠሙ ቆጨኝ።

በልቤ ውስጥ ያለው የውጊያ ሜዳም ቢሆን ጠቡ ከራሴ ጋር መሆኑ ሲገባኝ እጄን ሰጠሁ። ለውጊያው በግብአት የሚያገለግለውን የጥላቻ ስሜቴንም አሸነፍኩት። ከዚያም በዝምታ ውስጥ ቀስ በቀስ ለንዴቴና ለጥላቻዬ መልስ እያገኘሁ በሄድኩ ቁጥር እነዚያ ሕያው ይመስሉ የነበሩት የጥላቻ ዓመታት እንደ ዋዛ አለፉ። ከራሴም ጋር እርቅ አወረድኩ። በመጨረሻም የኢትዮጵያዊነትን እጅግ ውድ ስጦታነት ተገነዘብኩ። የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ከርሰ ምድር ውስጥ በከፍተኛ ድካም ተፈልጎ እንደሚገኝ አልማዝ መሆኑ ዘግይቶ ነበር የገባኝ። እኛነታችንን ፍለጋ እንድንባትል የሚያደርገን ነገር ሲያጋጥመን ክንዳችን በድካም ይዝላል፣ ከእውነቱ ፈቀቅ ብለን ለድካማችን ሰበብ እንፈጥራለን። ሰበባችን ጥላቻን ወልዶ ወደ ሌላ ክፉ ሀሳብ ተላልፈን እንሰጣለን።

የአስተሳሰብ ድህነታችን እንደ አልማዝ የሚያበራውን ውድና አንጸባራቂ ኢትዮጵያዊነታችንን ሲቀብረው እጅግ እንፈተናለን። ከኢትዮጵያ ምድር ደማቸው ተቀድቶ ሥጋቸው ተሠርቶ ፈጣሪ እስትፋንሱን "እፍ" ያለባቸው ሰዎች ሁሉ "Down Down Ethiopia (ኢትዮጵያ ትውደም ትውደም)" ለምን እንደሚሉ በእነርሱ

ጫማ ቆሜ ሕመማቸውን ለማዳመጥ እሞክራለሁ፡፡ አገራቸውን የረገሙት ልክ እንደ እኔ በራሳቸው ተናደው ስለመሆኑ ልብ የሚሉ አይመስለኝም፡፡ ስደታቸው እንደ እግር እሳት እየፈጃቸው ከኢትዮጵያ ጋር አእምሮአቸው ጦርነት የሚገጥሙ፤ ልቦቻቸው የውጊያ ሜዳ መልክ ይዞባቸው ባለማወቅ በራሳቸው ላይ የጥላቻ ናዳ የሚያወርዱ ሰዎችንና ስልፊኞችን ባየሁ ቁጥር ስቃያቸው ማለቂያ እንደሌለው አስብና ልቤ በብርቱ ያዝናል፡፡

"እያ እንቶኔ ነኝ!" ብዬ የምኮራበት የከፍታ ማማ ላይ እንድቆም ሊያደርገኝ የሚችል ስመ ማሕተም (prestige) የለኝም፡፡ በሰላም ሠርቶ ለማደር ከሚተጉ እልፍ አእላፍት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ነኝ፡፡ ይህም ሆኖ "ከአዙሪቱ ውስጥ ያልወጣነው ለድህነታችን ነገሥታቱን ተጠያቂ አድርገን በመቆማችን ይሆን?" ብዬም ራሴን ስጠይቅ ኖሬአለሁ፡፡ መልሱን ፍለጋ ወደ ዙፋኑ ተመለከትኩ፡፡

ዓይኖቼ የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ላይ አረፉ፡፡ ሳኦል እጁ በደም ሲጨማለቅ፤ ብቻውን የቆመውን እረኛውን ዳዊት ሲያሳድድ፤ የሰባውን ፍሪዳ ሲሰበስብ፤ በገዛ ልጁ ላይ ፈርዶ ጦሩን ሲወረውር፤ መንፈሱ በቅናት ሲታወክ፤ በውጊያ ውሎ በጠላት ሲከበብ፤ በራሱ ሰይፍ ላይም ሲወድቅ ሳይ ደነገጥኩ፡፡ ተሳዳጁ ዳዊት በተራው አሳዳጅ ሲሆን፤ ጠላቶቹን ሁሉ በውጊያ ሜዳ ድል ሲያደርግ፤ እጁ በደም ሲጨማለቅ፤በሠራዊቱ ብዛት ሲታበይ፤ በእስራኤልም ላይ መቅሰፍትን ሲያመጣባቸው፤ የታማኝ ወታደሩን የኦርዮ ሚስት ሲቀማ፤ ከጉልበቱ በወጡ ልጆቹ ሲታወክ፤ ልቡን ለነቢያቱ ምክር ሲሰጥ፤ የሊቃነ ሀገራትን ምክር ሲሰማ፤ ስለስሕተቱ ንስሀ ሲገባ፤ ዕድሜ ጠግቦም ሲያንቀላፋ ተመለከትኩ፡፡

ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን እጅግ ተወዳጅና ባለጸጋ ንጉሥ ሲሆን፤ ጥበቡን ለማየት የአረብ ነገሥታት፤ የኢሌኒ ንግሥትና ሌሎች ከሩቅ አገር የመጡ ነገሥታት በቤተመንግሥቱ ሲጋፉ፤ እጅግ የከበረ ውድ ስጦታ እጅ መንሻ ሲያቀርቡለት፤ ታላቁን ቤተመቅደስ ሲያሠራ፤ በጥበብ ሲፈርድ፤ በረቀቀ ፍልስፍና ጥበብን ሲመረምራት፤ እስራኤልንም ወደ ታላቅ ከፍታ ሲያወጣት በልቤ ተደነቅኩ። የሚገዛውን ሕዝብ በአለንጋ ሲገርፍ፤ ከወገኖቹ መካከል አገዛዙ አስመርሯቸው ወደ ግብጽ ምድር ሲሸሹ ተሳቀቅኩ። በጣኦት አምልኮ ከረከሱ ቆነጃጅት ጋር በፍቅር ሲወድቅ፤ ለስሙ መጠሪያ ሀውልት ሲያቆም፤ በመጨረሻም ሁሉም ነገር የከንቱ ከንቱ ሲሆንበት፤ ሲናዘዝም፤ የተሰጠው ጥበብ ሁሉ ኀዘኑን ብርቱ ሲያደርግበት፤ ሲተክዝም አብሬው ለመተከዝ በቃሁ። መልካም ሥራ ለዘላለም እንደሚኖር ሲመሰክር ሥራው ሁሉ እፁብ ድንቅ ሆነብኝ። ልጁ ሮብዓም በተራው ነግሦ በጓደኞቹ ምክር ሕዝቡን በጊንጥ ሲጋረፍ እጅግ ተገረምኩ።

ዘመን የማይሽረው የንግሥና ሥርዓት በቅርጽም በይዘትም ከጥንቱ ዘመን ጋር አንድ መሆኑን አስተዋልኩ። የእኛም ነገሥታት ደም ሲያፈሱ ተመለከትኩ። ሰይፋቸው ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ አሳድዶ ሲበላ፤ ሕያውነትን አጥብቀው ሲሹ፤ ከሞት ጋር ግብግብ ሲገጥሙ፤ ለሥራቸው ሀውልት ሲያቆሙ፤ ሀውልቶቹ ሲፈርሱ በዘመኔ አየሁ። ንጉሦች ጭካኔያቸውን ጥግ ድረስ ሲያሳዩን፤ ንጹሓን ዜጎችን በጅምላ በአንድ ጉድጓድ ሲቀብሩ፤ የአገራቸውን ሀብት ወደ ባዕድ አገር ሲያሸሹ፤ ሰውን ሁሉ በጎሳ ከረጢት ውስጥ ከትተው ኑሮውን የቁም ሲዖል ሲያደርጉት፤ የሚገዙትን ሕዝብ መንጋቸው ሲያደርጉት፤ መንጋውን በዙፋኑ ፊት እንደ ጣኦት ሲያሰግዱት ተመለከትኩ።

በዚህ ሁሉ የአስፈሪነት ድባብ የተከበቡ ነገሥታት በአንድ ነገር በብርቱ ሲደነብሩም አየሁ። ራሱን ችሎ ብቻውን በቆመ ሰው ነገሥታቱ በፍርሀት ሲርዱ፤ ዙፋኑን የከበቡ ጎሰኞችም ሲደነብሩ ተመለከትኩ። ፍርሀታቸውን ለመደበቅ ብቻውን የቆመ ሰው ካያለበት እያደኑ ሲያንገላቱት፤ ሲያስሩት፤ ሲያሳድዱት፤ ሲገድሉት፤ በእሳት ሲያቃጥሉት፤ ሲያኮላሹት አየሁ። ባዶ እጁን ብቻውን በቆመ ሰው ፊት ሲርበደበዱ አጃኢብ አልኩ። ልቤ አላረፈምና በደም በተነከረው ዙፋን ዙሪያ የነገሥታቱን መልካም ሥራ ፈለኩ። ጥቁርም ነጭም በተፈጥሮ የማይበላለጥ መሆኑ ያሳዩን፤ አገራቸውን የጠበቁ፤ ለአገራቸው አንገታቸውን የሰጡ፤ ትምህርት እንዲስፋፋ የተጉና በዓለም መድረክ በክብር የቆሙ ነገሥታት እንዳሉንም ተገነዘብኩ። ሊቃነ ሀገራት አገር ሲያረጋጉ የተጣሉ ሲያስታርቁ ንጉሡም ከልኩ አልፎ የሚገዛውን ሕዝብ እንዳያስመርር ሲመክሩትም ተመከለትኩ።

ወደሚገዙትም ሕዝብ ስመለከት ራሱን ችሎ መቆም ያቃተው ሰው አገሩን አምርሮ ሲራገምና ሲጠላም አስተዋልኩ። የማሕበረሰብ ቆስቋሾች መንጋውን ሲነዱት፤ መንጋው ነፃነቱን ከነፃ አውጪዎች ፍለጋ ሙዳዬ ምጽዋት በእጁ ይዞ ሲለምን በማየቴ ልቤ ክፉኛ አዘነ። በራሱ ሳንባ መተንፈስ አቅቶት እርሱነቱን ለባርነት አሳልፎ ሰጥቶ ብመለከት ግራ ገባኝ። ራሱን ችሎ የሚቆም ሕዝብ ባለበት አገር ነገሥታቱ የክብርና የኩራት ምንጭ ሆነው ሲፈነድቁባቸውም አየሁ። ዲሞክራሲ፣ ዘውዳዊ አገዛዝና ፌዴራላዊ ሥርዓቶች ልዩነት ሳያሳዩ ራሱን ችሎ የሚቆም ሕዝብ እንደ መሐጊል ቅንጣት አዋሕዷቸውና አስማምቷቸው ሕዝቡ በሰላም ሲኖር ተመለከትኩ። ብቻውን የሚቆም ሰው ያለነፍጥ የሕዝብ ልብ ሲገዛ አገሩን አጥብቆ ሲወድድ ተመለከትኩ። ይህን እይታ አጋራ ዘንድ ልቤ ቢሻ ይህችን መጽሐፍ ለመጦመር በቃሁ።

# ይህች መጽሐፍ መታሰቢያነቷ

እውነትን ይዘው ስለእውነት ሲሉ በታላቅ ሰብአዊ መንፈስ ራሳቸውን ችለው ብቻቸውን ለቆሙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይሁንልኝ!

# ምስጋና

ሕልሜ እውን እንዲሆን መንገዱን ላመላከተኝ ለወዳጄ ለቴዲ (ወልዩ)፤ ሐሳቤን ፈጥኖ ለተረዳኝ ለሰይፈዲን ሙሳ፤ መጽሐፉ ወግና መልክ እንዲኖረው ላደረገልኝ የልጅ አዋቂ ለሆነው ለደራሲ እሱባለው አበራ እንዲሁም አሸናፊ ቸኮል ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። የጃዕፈር ሺፋ ልዩ ድጋፍ ባይኖር ኖሮ እንደሌሎቹ ድርሰቶቼ ይህች መጽሐፍ በአንዷ ትንሽዬ ሱቅ የስኳርና ቡና መጠቅለያ በሆነች ነበር። ጃዕፈር ከልብ የመነጨ ምስጋና ይድረስህ።



# ተመስገን ጌታሁን

ደራሲው ተመስገን ጌታሁን በ 1953 ዋዜማ ጳጉሜን 3 በጥንታዊቷ ወሎ ግዛት ውስጥ ባቲ ከተማ ተወለደ ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ት/ቤት ባቲ ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በወ/ሮ ስኂን ትምህርት ቤት ተምሯል ።

የመጀመሪያ ዲግሪ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ፣ በድህረ ምረቃ አውዳዊ (ሕዝብ) አስተዳደር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተመርቋል።

በመንግሥት ልማት ድርጅት ( ተንዳሆ ) በአዲስ አበባ አስተዳደር መካከለኛው እርከን ፣ በግል አማካሪ ድርጅት ፣ በዓለም አቀፍ ድርጅት በግል ኩባንያ ጨምሮ ልዩልዩ ስራዎች ከጥጥ ለቃሚነት እስከ ከፍተ ኛ ኃላፊነት ስራ ተሰማርቶ ለ40 ዓመታት ያህል አገልግሏል ።

እንዲሁም በወቅታዊ የአገራችን ጉዳዮች በነፃ ፕሬሶች ከሁለት መቶ በላይ ጽሁፎችን አበርክቷል። ይኸው ጊዜው ደርሶ የመጀመርያ መጽሐፉን " ፋልስ " ሲል ሰይሞ ለንባብ አብቅቷል ::

መልካም ንባብ !!

ኢትዮጵያ ምድር አርባ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሦስት ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል። አንዱ ሥርዓት ሌላውን ስለሚኮንን የሰው ደም ሲፈስ ኖሯል።የዘውዳዊው ሥርዓት ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ በቆየባት አገር ላይ ደርግ የተከተለው የሶሻሊስት ሥርዓት ተዋውቆ ገና መሬት ሳይዝ ሌላ ሦስተኛ የብሔር ተኮር የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደ ብሉኮ በላይ በላዩ ላይ ሲደረብብን ሸክሙ አሁን ድረስ እጅግ አደርጎ ነው የከበደን። በተከታታይ የነገሡት ሁለቱ የደርግና የኢሕአዴግ ነገሥታት ያስተዋወቁት የሶሻሊስትም ሆነ የፌደራል ሥርዓት፤ የጬኹለትም የዲሞክራሲ ሥርዓት ለአገራችንም፣ ለእነርሱም እንግዳ ሆኖ ኖሯል።. ..አዳዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዳሳወቁን የሚተማመኑ እኒህ ነገሥታት ምንም ለውጥ ሳናይ እንደቀደሙት ነገሥታት ጸጥ ረጭ አድርገው ገዝተውናል። ..ዲሞክራሲና ኮሚኒዝም ሰዎች የማይኖሩበት ሕልም ሆኖ የቀረና የመከነ ሀሳብ ነው። ዘፋኑና ንጉሡ ናቸው የእኛን እጣፈንታ የሚወስኑት።


የሽፋን ገጽ ዲዛይን ስን DESIGN & ADVERT +251 913581340

ጃዕፈር መጻሕፍት | JAFAR BOOKS +251911125324

አታፍዘር አታሚዎች +251 929 90 81 08

ዋጋ 200 ብር